# የመለስ ራእይ ታላቅነት!

ዋለ አምባው 1/10/2013

የመለስ ራዕይ የሚለውን መልካምና ቅን ሀሳብ ባሻቸው የሚመነዝሩት ፅንፈኛ አክራሪዎችና በጥላቻ የተዘፈቁ ሰዎችን በየግዜው እያየን ነው፡፡ የወደዱትን ስያሜና ትርጉም እየሰጡ ሲሳለቁበትም እየተመለከትን ነው፡፡ ሲያሻቸውም የመለስ አምልኮ ሲፈልጉም ከሰማይ አማልክት ተርታ ወደ ማሰለፍም እንደፈጣሪ የመመለክ ሁኔታን እየፈጠሩ ነው ይላሉ፡፡ ከዚህም ባለፍ አዲሱም ጠ/ሚኒስትር ሆኑ ሌሎቹ ባለስልጣናት የመለስን ስም እያነሱ የታላቁን መሪ ራዕይ እናሳካለን ሲሉ ዛሬም ሀገሪቱ በመለስ ሙት መንፈስ የምትመራ ዓይነት አስመስለዋታል እያሉ በሀገር ውስጥ መፅሔቶችና ጋዜጦች እንዲሁም በውጭ ድረ ገፆቻቸው የማያነሱት የማይጥሉት ነገር የላቸውም፡፡ በሌላም መልኩ የመለስ ራዕይ ከሚሉ የኢሕአዴግ ራዕይ ቢሉ አይቀልም ነበር ወይ? ሁሉንም ነገር አዲሱን ቦሌ አይሮፕላን ማረፊያ ፣ ሕዳሴ ግድብን፤ ከዛም አልፎ የብር ኖቶችን፤ ሁሉ በታላቁ መሪ በመለስ ስም እናደርጋለን እያሉ ነው የሚልም አስተያየት ተፅፎ እያነበብን ነው፡፡ የነዚህ ወገኖች ችግር ምንድነው? የሚለውን በቅጡ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ ስለዚህም ወደ ዋናው ባህረ ሀሳብ መመለስ ግድ ይለናል፡፡

ይህንን ሀሳብ በዋነኛነት እያቀነቀኑ ትችትና ነቀፌታ የሚስነዝሩት ክፍሎች የመጀመሪያው መነሻ ምክንያታቸው ጭፍንና ገድብ የለሽ ጥላቻቸው ሲሆን ሌላው ደግሞ ሕዝቡ ዘንድ ሰርፆ የገባውና የጠ/ሚ መለስ ዜናዊ በህዝብተቀባይነት፤ የኢሕአዴግም በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ስለሆነ ይህ መስረታዊ ጉዳይ የእነሱን ተቀባይነት ስለሸረሸረው ከፍተኛ የመንፈስ መረበሽ ውስጥ ወድቀዋል፡፡ በፍርሀትና በጭንቀት ተውጠዋል፡፡እየራዱም ይገኛሉ፡፡ ይሄንን ግዙፍ ሕዝባዊ ተቀባይነት ለመቀነስ ወይንም ለመሸርሸር ይጠቅመናል ብለው የያዙት መንገድ የመለስ ራዕይ የሚለውን ሀሳብ ያለመታከት በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ለማናናቅ ለማጥላላት ለማጣጣል ጥረት ማድረግ ነው፡፡

የመለስ ስም በተነሳ ቁጥር የሚታመሙበትም ምክንያት ይኸው ነው፡፡ ሌላማ የመለስም ሆነ የኢሕአዴግ ራዕይ አንድ መሆኑ አይጠፋቸውም፡፡ መለስ ማለት ኢሕአዴግ፤ ኢሕአዴግም ማለት መለስ እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ሁል ጊዜም መሪዎች በታሪክ ውስጥና በሂደቱ የየራሳቸውን ልዮ አሻራና ማሕተም ጥለው እንደሚያልፉ በኢትዮጵያም በዓለምም ይታወቃል፡፡መሪዎች እድገትን በማፋጠን ወይንም በማዘግየት የየራሳቸው ግለሰባዊ ሚና አላቸው፡፡

አንዱ መሪ ከቀደመው ወይንም ከሌሎች የሚለይበት እሱነቱን የሚያጎላው ወይንም የሚያደበዝዘው የራሱ መለያ ባሕርያትም አሉት፡፡ በሕዝቡ የሚወደስበት፤ ስብዕናው የሚጎላበት፤ በልዩ ሁኔታ የሚታወሰበትና የሚዘከርበት አሊያም ደግሞ የሚጠላበት ሁኔታዎች አሉ፡፡ የመለስ ራዕይ ወደኋላ ዘርዘር አድርገን ብናየውም በአጭሩ ቋንቋ ሲገለፅ ከድህነት ከልመና ለመውጣት ጠንክረን እንስራ! ሀገራችንን እናልማ! እናበልፅግ! የተከበረችና የታፈረች፤ በሁሉም መስክ አቅሟ የጎለበተ፤ ለጠላቶቿም የማትንበረከክ ታላቅ ሀገር እናድርጋት! ነው፡፡ ይሄ ራዕይ ምኑ ነው መጥፎነቱ? ምኑስ ላይ ነው የሚነቀፈው? ምኑስ ነው የሚጠላው?

ዛሬ የመለስ ራዕይ (የኢሕአዴግ) ራዕይ ከኢትዮጵያ ድንበር ተሻግሯል፡፡ የድፍን አፍሪካ ራዕይ ሆኗል፡፡ ከዚህም ልቆ ሄድዋል፡፡ በመላው ዓለም ያሉ ታዳጊ ሀገሮች ራዕይ ሆኗል፡፡

የተፈጠሮ ሀብታቸውን፤ እውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ተጠቅመው እያላቸው የሌላቸው ሁነው ተረጂና ተመፅዋች ከመሆን በመላቀቅ፤ ራሳቸውን የሚችሉበት ከድህነት የሚወጡበት፤ ለዚህም የመረረ ትግል የሚያደርጉበት ግዙፍና ታላቅ ራዕይ ነው፡፡ይሄ ራእይ ወደድንም ጠላንም ድንበር ተሻግራል፡፡ከእኛ አልፎ የአፍሪካ ራእይ ሆናል፡፡ ሀገራት ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው የተፈጥሮ ሀብታቸውን በሌላ የውጭ ኃይል ሳያስመዘብሩ፤ ነፃነታቸውን አሳልፈው ሳይሰጡ፤ በሰላምና በመከባበር ላይ የተመሰረተ፤የእውቀትና የልምድ ልውውጥ በማድረግ ሀገራችውን የሚያለሙበት፣ የሚያሳድጉበት፤ እርዳታ ጠባቂ ከመሆን የሚወጡበት ራዕይ ነው፡፡

ይህ ደግሞ የሚነቀፍ ሳይሆን በሙሉ ልብ የሚደገፍ በሙሉ ትጋትም ሕዝቦች ፀንተው ቆመው የሚሰሩለት ነው፡፡ፅንፈኛው ተቃዋሚ፤ የሀገር ቤቱ ተቃዋሚ ሊነቅፈው፤ ሊተቸው፤ ሊያጣጥለው፤ እንደሚሞክረው ሳይሆን (የዚህ ምክንያቱ ከላይ ተገልፃል) የመለስ ራዕይ ወይንም የፓርቲው የኢሕአዴግ ራዕይ ሀገሪቱን ከጨለማ ወደ ብርሃን የሚያሸጋግር፤ ከድህነት ወደ ብልፅግና እንድታመራ ለውጦቹና የተመዘገቡት ድሎች የሚታዩ በመሆናቸው ይህ ታላቅ ራዕይ የእያንዳንዱ ሀገሬን እወዳለሁ፤ ልማትዋን እመኛለሁ የሚል እውነተኛ ዜጋ ሁሉ ራዕይ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

ይህንን ታላቅ ሀገራዊ ራእይ የሚቃወሙ ሰዎች ወይንም ቡድኖች እኛ ልንመራው ይገባ ነበር የሚል ተራ የቅናት መንፈስ ውስጥ ከመግባታቸው የመነጨ ሀሳብ እንጂ በእውነቱ የሚቃወሙት ወይንም ሊቃወሙት የሚገባ ሁኖ አይደለም፡፡ የመለስ ራዕይ (የኢሕአዴግን ራዕይ ) ሲቃወሙ ምንንና ማንን ነው እየተቃወሙ ያሉት? የመሰረተ ልማት ግንባታውን? የሀገሪቱን መንገድ እጅግ

በዘመነ መንገድ መስፋፋት ? አየር መንገዳችን በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ከአየር ማረፊያው ጀምሮ መስፋፋቱና በአፍሪካ ሰማይ ብቸኛው የጀት ድሪምላይነር ባለቤት መሆኑን?

የመለስን (የኢሕአዴግን) ራዕይ ለምንድነው የሚቃወሙት? ኢትዮጵያ በርካታ የኃይል ማመንጫ ግድቦች መገንባትዋን? በታሪክ ያልተሞከረውን የሕዳሴውን ግድብ በራሳችን አቅም ለመገደብ ቆርጠን መነሳታችንን? ስራውን መጀመራችንን? በኢትዮጵያ አዲስ የሆነውን የንፋስ ኃይል ኃይል ማመንጫ የጂኦ ተርማል ተጠቃሚ መሆናችንን? የኢትዮጵያ መንገድ ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መንገድ ተስርቶ ፤በሰሜን እስከ ካይሮ ፤በደቡብ ከኬንያ እስከ ኬፕ- ታውን፤ በምዕራብ እስከ ካርቱም፤ በምስራቅ ጅቡቲና ሶማሊያ ድረስ ሊዘልቅ በሚችል ደረጃ ታቅዶ ስራው መጀመሩን?

እኮ ምኑን ነው ይህን የመለስን ራዕይ የፓርቲውን የኢሕአዴግን ራዕይ የሚቃወሙት? በኢትዮጵያ በርካታ ዩኒቨርስቲዎች ኮሌጆች መገንባታቸውን? ዜጎችን የቤት ባለቤት ለማድረግ መንግስት የኮንደሚኒየም ቤት እየሰራ በእጣ ማከፋፈሉን? ዘመናዊ የባቡር አገልግሎት በአዲስ አበባና ክልሎች እንዲዳረስ፤ የጅቡቲ አዲስ አበባም መሰመር በአዲስ ቴክኒዮሎጂ መሳሪያ ተገንብቶ አገልግሎት እንዲሰጥ የተፋጠነ ስራ በመሰራት ላይ መሆኑን? የትኛውን ነው የመለስን/ የኢሕአዴግን ራዕይ የሚነቅፉት ? ኢትዮጵያ ጠንካራና ዘመናዊ የመከላከያ ኃይል በመገንባት፤ በራሷም አቅም ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ለማምረት መብቃትዋን ? ዘመናዊና ብቁ አየር ኃይል መገንባቱን? በአፍሪካ ቀንድ በምስራቅ አፍሪካ ባሉ ሀገሮች ልእለ ሀያል አገር ለመሆን በመብቃትዋ? የመሬት መሸርሸርንና የደን መጨፍጨፍን በመግታት፤ የተራቆቱት ደኖች በደን እንዲሸፈኑ በማድረግ በረሀማነቱን ለመከላከል በወሰዳቸው እርምጃዎች ያመጣችውን ለውጥ?

የቱን ነው የመለስን ራእይ የሚያጣጥሉት? በፈጠነ ሁኔታ ትውልድንና ሀገርን እየጨረሰ የነበረውን የኤች አይቢ ኤድስ ወረርሽን ተረባርቦ በመግታቱ? ትምህርትን ከሙያዊ እውቀት ጋር በማቀናጀት ክህሎት ያለው ዜጋ ለመፍጠር በቴክኒክና በኢንፎርሜሽን ቴክኒዮሎጂ ላይ ያተኮረ ትውልድ ለመፍጠር ርብርብ በመደረጉ? በርካታ የልማት ድርጅቶች በመገንባታቸው? በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች የሞባይል ቴሌፎን አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመደረጉ? በገጠርም ኤሌክትሪፊኬሽን ገጠሩን በኤሌክትሪክ ብርሀን የማዳረስ የዘመቻ ስራ በመሰራት ላይ መሆኑ?

በአጠቃላይ ራሷን የቻለች ከተረጅነትና ከረሀብ የተላቀቀች፤ የጥንት ስሟንና ክብሯን ለመመለስ በተሀድሶ ሂደት ላይ መሆኗ መገኘትዋ? እነዚህ ሁሉ የመለስ ወይንም የኢሕአዴግ ራዕይ ተብለው የሚጠቀሱና የሚገለጡ ናቸው፡፡ ከዚህም  በላይ ርቆ ይሄዳል:: ትውልድ ራእዩን እያገዘፈው

ይሄዳል፡፡ገና ገና ይተማል፤ይገሰግሳል እንጂ መች ይቆማል? ይህን ራእይ የአገርን እድገት የሚቃወም እንዴትስ ነው ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው? በአጭሩ ሲሰበሰብ በሁሉም መስክ ብቁ የሆነች በኢኮኖሚ እድገት የበለፀገች፤ከድሕነት የተላቀቀች ፤ ከተረጂነት የወጣች፤ ዜጎች በሙሉ በዘመናዊ እውቀት የታነፁና የተገነቡባት ፤ ያለ አንዳች የውጭ ኃይል ጣልቃ ገብነት በራሷ አቅምና በሕዝቧ የተማመነች ሀገር፤ በሥልጣኔና በእድገት የገፋች ሀገር እንድትሆን ማስቻል ነው የመለስ ራዕይ ወይንም የኢሕአዴግ ራዕይ ፡፡

ይህንን ታላቅ ሀገርንና የትላንት የድህነት ታሪካችንን ተረጂነትና ተመፅዋችነትን ሙሉ በሙሉ በስራ ታግሎ አሸንፎ ለመውጣት የተሰነቀውን ራዕይ፤ የሀገራችንና የሕዝባችን ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ ተቃዋሚዎች እንዴት ነው የሚቃወሙት? የሀገራችውን ልማትና እድገት፤የሕዝቡንም ኑሮና ህይወት መለወጥ አይፈልጉትም ማለት ነው? ወይንስ የመለስ ወይንም የኢሕአዴግ ስም ሲነሳ ምንም መልካም ይሁን ምንም ከመቃወምና ከማጥላላት አንመለስም በሚለው የጥላቻ ፓለቲካ ውስጥ እየዋኙ ስለሚገኙ ነው? በዚህ መልኩ አገርን ማሳደግ እንዴት ይቻላል? በመሰረቱ የመለስ አምልኮ የሚባል ነገር የለም:: መለስ የሚወደሰው፤የሚደነቀው በአስተሳሰብ ምጥቀቱና ብስለቱ፤ አዳዲስ ሀሳቦችን ሌሎች ሊመለከቱት በማይችሉበት ጎን ከነመፍትሔው ማቅረብ በመቻሉ ነው፡፡ለእውቀትና ለሥራ የነበረው ጥልቅ አክብሮትና ፍቅር፤ ሀገሩን ከድህነትና ከኃላቀርነት ታግሎ ለማውጣት ወደ በለፀገች ሀገርነት ለመለወጥ ያፈለቀውን፤ አዲስ ውጤታማ የተግባር መርሀ ግብሮችንና አፈፃፀማቸውን ቀምሮ ለማውጣት በመቻሉነው፡፡

ጠንካራ ሀገር፤ ጠንካራ መንግስት ፤ ጠንካራ ኢኮኖሚ ፤ ጠንካራ መከላከያና ደህንነት ፤በርካታ ተቋማት፤ ዩኒቨርስቲዎች፤ ግድቦች፤ ኃይል ማመንጫዎች፤ የመከላከያ ፋብሪካዎች የመከላከያ አንጂነረንግ፤ ከድሮው መሰረት በመነሳት የዘመኑን ቴክኒዮሎጂ በእጁ ያስገባ የድሪም ላይነር ጀት ባለቤት የሆነ አየር መንገድ እንዲኖረን በማድረጉ ነው፡፡

የረቀቀ የዲፕሎማሲ ብቃትና ችሎታውን ከኢትዮጵያ አልፎ ለድፍን አፍሪካ ተወካይነትና መሪነት፤ በዓለምም ደረጃ በምዕራባውያን መንግስታትት ዘንድ ታላቅ ክብርና ሞገስ ያገኘ ኢትዮጵያን ያኮራ፤ ያስከበረ፤ ምሁር ዲፕሎማትና የጦር ጠብብትም ነው፡፡ ከሁሉ የሚገርመው በእውቀቱ ያልተበየ ፤ያልተኩራራ፣ ስራዬን እውቁልኝ ያላለ ግን ሕዝብና ታሪክ የመስከረለት ሰው ነው፡፡

አንድም ቀን እኔ ብሎ ሳይናገር ያለፈ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰዎች ብዙ የሉም፡፡ በጥቂቱ ስራቸውን የሚያገዝፉ የሚኩራሩ ብዙ ሰዎችን አይተናል፡፡ የእኛ ባሕል ደግሞ ያለመታደል ሁኖ

የውጭ ሰዎችን (ነጮችን) ማድነቅ ፣ የእነሱን ገድል ማውራት ፤ ስለነጮች መጻፍ ፤ፍቶዎቸውን አሳድጎ መስቀል ፤የእነሱን ንግግር በጥቅስ መልክ መናገር፤ በእነሱ ሙዚቃና ዘፈን መደነስ መጨፈር ማውካካት ስልጣኔና አዋቂነት የሚመስላቸው ብዙዎች ናቸው፡፡ ገፉ ብለው በምሁሩ ተርታ ያሉትም ጭምር፡፡

በቅኝ ግዛት ያልኖርን ባርነትን የማናውቅ በእኛነታችን በአበሻነታችን በባህላችን በታሪካችን በጀግኖቻችን የምንኮራ ነበርን፡፡ነንም፡፡ ከሌላው ሀገር ፈላስፋ አዋቂ ምሁር ጀግና በለውነቱ ከእውቀቱ የምንካፈለው የምንወሰደው ቢኖረንም ኢትዮጵያውያንም ከሌሎች ዓለም ሰዎች እኩል የተሻለ ወይንም የበለጠ እውቀት ምጥቀት ሊኖራቸው እንደሚችል እንዳለንም በመገንዘብ በራሳችንና የራሳችን በሆነው ሁሉ መኩራት አለብን፡፡

እንደ መሪ ጥንት የነበሩትም የኢትዮጵያ መሪዎች አነሰም በዛም ዘመኑ ባይሰለጥንም ለሀገራቸው ራዕይ ነበራቸው፡፡ የአክሱም ስልጣኔ ከጥቂቶች በቀር ዓለም በጨለማ ውስጥ በነበረችበት ሰዓት እንደነባይዛንቲን ኢምፓየር ሁሉ ብርሀንና እውቀት የፈነጠቀ ገናና ስልጣኔ ነበር፡፡

የጥንት የኢትዮጵያውያን ስልጣኔ ለመጀመሪያ ግዜ ብረት ማቅለጥና ለስራ ማዋልን፤ የመገበያያ ፍራንክ መፍጠርን፤ መደበኛ ስራዊትን አቋቁሞ በደመወዝ ማሰራትን ፤የብዙ መርከቦች ባለቤት በመሆን ከቀይ ባሕር እሰከ ዘይላና በርበራ እሰከ የመንና የዛሬዋ ሳውዲ ዐረቢያ ድረስ ተቆጣጥሮ ይመራ ያስተዳድር የነበረው ነው፡፡ በታሪክ ተፅፎ ይገኛል፡፡ ከግብፅ ፈርኦኖች ውስጥም ኢትዮጵያውያን ነበሩበት፡፡ የአክሱም ሀውልት አስራር ምስጢር እሰከ ዛሬ አልተፈታም ፡፡ክሬንና ኮምፒዩተር እንደ ዘመናችን ኢንጂነር በሌለበት ያንን ድንቅ ሀውልት ኢትዮጵያውያን በዛን ዘመን እንዴት ሰሩት? የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፤ የጎንደር ቤተመንግስትና ጥንታዊ ስልጣኔ፤ በዛ ሩቅ ዘመን ለኢትዮጵያውያን ቀደምት የስልጣኔ ባለቤትነት ዘመን ተሻግረው የሚያወሩ የሚናገሩ ምስክሮች ናቸው፡፡

ያ ሁሉ ገናና የጥንታዊ ስልጣኔ ታሪክ አልፎ በዓለም ቀዳሚ ከሚባሉት ጥቂት ሀገሮች አንዷ የነበረችው፤ የስልጣኔና የሰው ዘር መገኘዋ ኢትዮጵያ ሁሉንም አጥታ፤ ታሪኳም ክብሯም ጠፍቶ የድህነት የረሀብ የተረጂነትና የተመፅዋችነት ስም ተከናንባ ለመኖር ተገድዳለች፡፡ የእርስ በእርስ ጦርነትና ሽኩቻ የስልጣን ግዛት ቅርምት ሀገሪቷን ገድሎአት ኖረ፡፡ ሌሎች ቀደምት የኢትዮጵያ መንግስታት የቱንም ያህል ራዕይ ለሀገራቸው ቢሰንቁም ግዜና ታሪክ ሳይፈቅድላቸው ቀርቶ አለፈ፡፡

የሩቁን ትተን ከአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ የተነሱት አፄ ቴዎድሮስ አገር አንድ አደርጋለሁ ብለው ላይ ታች እንደተንከራተቱ አለፉ፡፡ አፄ ዮሀንስም ከድርቡሽ ወራሪ ጋር ሲዋጉ መተማ ላይ ተሰው፡፡ እምዬ ምኒልክ የስልጣኔ ጭላንጭል የታያቸው የቴዎድሮስ ግርፍ ስለነበሩ የጋዜጣ ጅምር የትምህርት ቤት ጅምር፣ ስልክ፣ መኪና ፣ ባቡር ፣የመሰለውን በትንሹም ቢሆን ለማስገባት ሞክረው ጥሩ መሰረት ጣሉ፡፡ ቀደም ሲል ወራሪውን ጣሊያን በአድዋ ጦርነት ድል አድርገው ለአፍሪካም ለዓለምም ሲናቅ የነበረውን የጥቁር ሕዝብ ጀግንነት አረጋግጡ፡፡ አፄ ኃይለ ስላሴ በለስ ቀንቶአቸው የአዲሲቷን ኢትዮጵያ የስልጣኔ መሠረት በመጣል ይኽ ቀረሽ የማይባል ስራ ሰሩ፡፡ ኢትዮጵያንም ከዓለም አስተዋወቋት ፡፡ ደርግ በጦርነት ውስጥ ኖሮ አለፈ፡፡

እንግዲህ የመለስ ራዕይ ወይንም የኢአሕዴግ ራዕይ ብለን የምንጠራው ታላቅና ግዙፍ ራዕይ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ክብርና ገናናነት ለመመለስ፣ የተሀድሶ ዘመን ለውጥ በመምራት፣ የወደቀ ሰሟን ለማንሳት፣ የጨለማ የረሀብተኛና ተመፅዋችነት ታሪካችንን ለመለወጥ፣ በታሪካቸን ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ መልኩ የሚታይና የሚጨበጥ ግዙፍ የኢኮኖሚና የእድገት ለውጥ እያስመዘገበ ያለው፡፡ የመለስ ራእይና አምልኮ በሚል ለጻፉትና ለሚፅፉት ግለሰቦች፣ ለሀገራቸው ክብርና ለሕዝባቸው ያላቸው ፍቅር፣ ለሀገር ልማትና እድገት የሚሰጡት ቦታ ሁሉ በከባድ ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል፡፡ የመለስ ወይንም ኢሕአዴግ ራዕይ ኢትዮጵያን ከድህነትና ከኃላቀርነት፣ ከተረጂነትና ከተመጽዋችነት በማውጣት ራሷን የቻለች፣ ለራሷ የበቃች፣ ለልጆቿ የተመቸች፣ በስልጣኔና በእውቀት የላቀች ሀገር ማድረግ ነው፡፡

በአፍሪካም በዓለምም የተከበረች ተዳማጭ የሆነች ኢትዮጵያን መፍጠር ነው፡፡ የመለስም ሆነ የኢሕአዴግ ራዕይ በዘመናዊ እውቀትና ክህሎት የታነጸ ፣የተገነባ ፣ለሀገሩ ተስፋና አለኝታ የሆነ ሥራ ፈጣሪ ፣ የፈጠራ ችሎታ ያለውና ያዳበረ ተመራጭ ብቁ የሆነ፣የነገዋን ኢትዮጵያ ተረካቢ ትውልድ መፍጠር ነው፡፡ መሪዎች የሚመሩትን ፓርቲ ድርጅት ወይንም መንግስት ይወክላሉ፡፡ መለስ ዜናዊ የኢሕአዴግ ሊ/መንበር የኢትዮጵያ መንግስትም ጠ/ሚኒስትር ነበሩ፡፡ የመሪው ራዕይ የፓርቲውም የመንግስቱም ራዕይ መሆኑ አያከራክርም፡፡ መለስ ከፓርቲው ጋር ለኢትዮጵያ እድገት የዘመናችንን ታላቅ ራዕይና ግቦች ጀምሮት፣ አስጀምሮት መጨረሻውን ለማየት ሳይታደል በድንገት አለፈ፡፡

ይኸንን ለሀገር እድገትና ልማት የተሰነቀ ግዙፍ ራእይ ማሳካትና ከዳር በማድረስ በውጤቱም ተጠቃሚ የሚሆነው ሕዝብና ሀገር ነው፡፡ ራዕዮን በማሳካትና በእቅዱ መሰረት መጓዙን ፣ሳይሰተጓጎል መቀጠሉን፣ የመቆጣጠር የመከታተልና የማትጋት የመሪነት ስራና ተግባሩ ደግሞ የመንግስትና የኢሕአዴግ ነው የሚሆነው፡፡ ይኸም ተግባር እየተሰራና እየተከናወነ ይገኛል፡፡

አገሪቱን በአዲስ የእድገትና የልማት ጎዳና ሙሉ በሙሉ ሰርነቀል በሆነ ደረጃ የመለወጡን ሀሳብ አመንጭቶ ኢሕአዴግም ተወያይቶበት ሀሳብ ሰጥቶበት ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ ሲያፀድቀው ወደ ተግባርም ሲመነዝረው ራዕዮ የመለስ የግል ብቻ ሳይሆን የኢሕአዴግ ራዕይ ሆነ ወይንም ይሆናል ማለት ነው፡፡

የፓርቲ አሰራር በየትም ዓለም ይኸው ነው፡፡ አገርን በትልቅ ደረጃ የሚለውጥ ድንቅ ሀሳቦች የሚመነጨው ከመሪውም ከአባላቱም ሊሆን ይችላል፡፡ በጠንካራ ውይይት ሀሳብ ፍልሚያ ይደረግባቸዋል፡፡ ትችት ይሰነዘራል፡፡ ተቃውሞ ይቀርባል፡፡ አያስፈልግም ባለው ሀሳብ ሁሉም ካመነበት ውድቅ ይደረጋል፡፡ ሌሎች ጠቃሚና አጋዥ አዲስ ሀሳቦች ቀደም ብለው በሌላ ጎኑ ያልታዩ አማራጮች ሲገኙ ይታከሉበታል፡

ከፓርቲው አልፎ ሙያተኞች ኤክስፐርቶች አበጥረው ይመክሩበታል ይወያዩበታል፡፡ የራሳቸውን ተሞክሮና ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡ የጎደለው ጎን ከፍተት ፤ አደጋ፤ኪሳራ፤ ካለው በውስጥና በውጭ የሚፈጥረው ሂደት ይመረመራል፡፡ ከአዛውንቶች ልምድና ከተሞክሮም ሀሳብ ይሰበሰባል፡፡ የመጨረሻው መጨረሻ ራዕዩ ተምኖበት ከጸደቀ ወደ ተግባር ለመለወጥ የገንዘብ አቅም ይፈለጋል፡፡ እናም ወደ ስራ ወደ ተግባር ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ ነው የመለስ ራዕይ ወይንም የኢሕአዴግ ራዕይ ዓይናችን እያየ ኢትዮጵያን ወደ ተሻለች ሀገርነት እየለወጣት ያለው፡፡ አንዳንዱ በጭፍን ጥላቻ የተዋጠ ተቃዋሚ ፤ኢትዮጵያን እኛ ካልመራናት በስተቀር የመለስም ኢሕአዴግም ራዕይ አይሰራም ባይ ነው፤ እንደሚሰራ እያየውም ጭምር ይክዳል፡፡

ሌላው ሀገሪቱን ለማሳደግ የታቀደው የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን መሪ እቅዱ ግዙፍና የተለጠጠ፤ በስሜትና በፍላጎት የተቀረጸ ስለሆነ ከወረቀት አያልፍም ፤በተግባር አናየውም፤ ይኸን ለማሳካት አንዲት ድሀ አገር ይኸን ግዙፍ ገንዘብ የማግኘት አቅም የላትም ፤ ኢሕአዴግ የሕዝቡን ስሜትና ቀልብ ለማነሳሳት እንጂ አይሰራውም ሲሉ ከረሙ፡፡ ማንም ምንም አለ ስራው እየተሰራ ነው፡፡ የሕዳሴው ግድብ እንኳን ተጀምሮ በራሳችን አቅም 13% ያህል ተጠናቋል፡፡

የመለስ ራዕይ ለሀገር እመርታዊ ለውጥ የሚያስገኝ ታላቅ ራዕይ ስለሆነ ነው የሚወደሰው፤ የሚከበረው፤ የሚደነቀው፤ ጠዋት ማታ የሚነገርለት እንጂ ማምለክ አይደለም፡፡ መለስ ለራሱ ሳይኖር እኔ ሳይል ኑሮ ያለፈ ሰው ነው፡፡ የአክራሪ ተቃዋሚው ትችት ሀገሪቱ በመለስ ሙት መንፈስ የምትመራ አስመስሎታል፤ ባለሥልጣናት የመለስን ራዕይ እናሳካለን ብለው ካልተናገሩ የተናገሩ አይመስላቸውም፤ በመለስ ስም አውሮፕላን ማረፊያ፣ ተቋም፣ብር ኖት እንሰይማለን እያሉ ነው ይላሉ፡፡

መለስ ካለፈ ገና አራት ወሩ ሲሆን ለኢትዮጵያ እድገትና ስኬት የሰነቀው ራዕይና ስሙ ገና ብዙ ኢትዮጵያዊ ትውልዶችን እየተሻጋገረ ይተላለፋል፡፡ ለሀገርና ለሕዝብ ታላቅና ዘመን ተሻጋሪ ስራ ሰርቶ ላለፈ ሰው፤ ከመቃብር በላይ ሕያው ሁኖ የሚኖር የሀገር ቅርስና ውለታ ጥሎ ላለፈ ጀግና፤ ታሪኩ የሚዘከርበት ሰሙ የሚታወስበት የተለያ መታሰቢያ ቢተከልለት ምንድነው ነውሩ? ምንም ስህተት የለውም፡፡ በዓለምም ላይ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ሀገራት ሁሉ ራዕይ የነበራቸውን መሪዎቻቸውን ጀግኖቻቸውን ያወድሳሉ፤ መታሰቢያ ሀውልት ያቆማሉ፤ ተቋም ይሰይሙላቸዋል፤ ታሪካቸው በመፅሀፍት ይወጣል፡፡ ፊልም ይሰራላቸዋል፡፡ ቀን ወይንም ከተማ ይሰየምላቸዋል፡፡ የብር ኖትም ያሳተሙ አሉ፡፡ ምንም አዲስ ነገር የለም፡፡

አዲሱ ጠ/ሚኒስትር ክብር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ከተሾሙበት ግዜ ጀምሮ በየትኛውም ንግግራቸው ላይ የታላቁን መሪ ራዕይ እናሳካለን ነው የሚሉት እንደ መሪ ከመለስ የተለየ የራሳቸው ራዕይ የላቸውም ወይ? ለሚሉትም ስራ ፈት ተቺዎች የመለስ ራዕይ የ80 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ራዕይ፤ በሁሉም መስክ የአገር ምጥቀት ራዕይ በመሆኑ ኃይለማርያም ደሳለኝ እንደ ዜጋም ሆነ እንደ መሪም ከዚህ የተለየ ምን ራዕይ ይኖራቸዋል?

መለስና ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን ታላቅ የማድረግ ራዕያቸው እንደተባለው በቅብብሎሽ ከትውልድ ትውልድ እያለፈ የሚቀጥል የቤት ስራ እንጂ በአንድ ዘመን የሚቋጭ አይደለም፡፡የመለስ ራዕይ በሚል አጭር ቋንቋ የሚገለፀው የመለስ ራዕይ በኢኮኖሚው፣ በቴክኒዮሎጂው፣ በኃይል ማመንጫው ፣ በግድብ ግንባታው፣ በንፋስ ኃይል ማመንጫው፤ በከባድ ኢንዱስትሪ ፤ በመከላከያ ፤ በመንገድ ስራ ግንባታው ፤በሀገር ውስጥ ያሉ ከተሞችንና አልፎም ጎረቤት አገሮችንና አፍሪካን የሚያቋርጥ መንገዶችና ዘመናዊ ባቡር አገልግሎት መስመር መዘርጋትና ግንባታውን ያካትታል፡፡ ኤሌክትሪክ ኃይል ከኢትዮጵያ ወደውጭ ሀገራት በመሸጥ ለኢትዮጵያ ታላቅ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ማስገኘቱ፣ የማዕድናትና የራሳችንን ነዳጅ ፈልጎ የማውጣት ስራው ፣ የኢትዮጵያን የተራቆተ መሬትና ተራራ በደን ልማት የመሸፈኑ እቅድና ስራ፤ግብርናውን ከባህላዊ አስተራረስ የማውጣትና ዘመናዊ ውጤታማና ትርፋማ የማድረጉ፣ የራሳችንን ባቡር የራሳችንን የጦር መሳሪያ ለመስራት ውጤታማ ስራ መስራቱ፤የራሳችንን ሄሊኮፕተር፤ አውሮፕላን፤ጀት ወደ ምንሰራበት ደረጃ ልንሸጋገርም እንችላለን፡፡እነዚህንም አቅፎ ይይዛል፡፡

በምግብ እራሳችንን ለመቻል ከተረጂነት ለመውጣትመስራትና ሌሎችንም በስፋት ያካትታል፡፡ ይህ ራእይ ዘመን ተሻገሮ ይተላለፋል፡፡ ለሀገርና ለሕዝብ ታላቅና ዘመን ተሻጋሪ ስራ ሰርቶ ላለፈ ሰው፤ ከመቃብር በላይ ሕያው ሁኖ የሚኖር የሀገር ቅርስና ውለታ ጥሎ ላለፈ ጀግና ፤ታሩኩ

የሚዘከርበት ሰሙ የሚወሳበት የተለያየ መታሰቢያ ቢተከልለት ምንድነው ነውሩ? ምንም ስህተት የለውም፡፡ በዓለምም ላይ አዲስ አይደለም፡፡ በምግብ እራሳችንን ለመቻል ከተረጂነት ለመውጣትና ታሪካችንን ካጎደፈው ተመፅዋችነት ለመላቀቅ ፤የተጀመረው ራስን የመቻል ስታራቴጂና የቁጠባ ባህል፤ የጠና አገልግሎትን በድፍን ኢትዮጵያ ከተማና ገጠር ለማድረስ የተዘረጋው እቅድ፣ በመከላከል ላይ ያተኮረው የኤች አይቪን ስርጭት በአስደናቂ ሁኔታ የገታው የጤና ፖሊሲና፤ ጤና ለሁሉም ፕሮግራም፤የአርብቶ አደሩን ተንከራታች ሕይወት ትርጉም ባለው ሁኔታ መለወጥ መቻሉ የራእዩ አካል ናቸው፡፡

ውሀ በአለበት አካባቢ በቁፋሮ በማውጣት እርሻ እንዲጀመር ማስቻሉ፤ በትምህርት ፓሊሲው በሀገሪቱ በርካታ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች መከፈታቸው ጥራቱ በሂደት ይጎለብታል፤ በውጭ ኃይሎች ተፅእኖ ስር የማትንበረከክ ጠንካራ ኢኮኖሚና መሰረተ ልማት ያላት ሀገር የመፍጠሩ ስራ ፤በአፍሪካም በዓለምም የተከበረችና ተደማጭ ኢትዮጵያን በሂደት ለመፍጠር የታየው ጅምር፤ ከተሞቻችንን እጅግ ዘመናዊ ለማድረግ የተጀመረው የትላላቅ ሕንፃዎች ግንባታ፤ ዜጎችን የቤት ባለቤት ለማድረግ የተጀመረው ተከታታይ የኮንደሚኒየም ቤቶች ግንባታ፤ የተለያዩ የምርምር ማዕከላት ማቋቋሙ እና ሌሎችም ያልተገለፁ በርካታ ዓቢይ ጉዳዮች ሁሉ በመለስ ራዕይ ውስጥ ያሉና የተካተቱ ናቸው፡፡
ፓርቲው ኢህአዴግ ወይንም መንግስት የመለስ ራዕይ የሚል ለኢትዮጵያ የነደፈውንና ያቀደውን ታላቅ የእድገት ግቦች በዝርዝር የሚገልጽ መፅሀፍ ማሳተምና ለሕዝብ ማድረስ አለበት፡፡ ይህ ሲሆን የመለስ ራዕይ ሲባል የሚፈጠረው የአልገባቸው ሰዎች መደናገር ወይንም እያወቁ እንዳላወቁ የሚተቹና መሳለቅ የሚወዱ ክፍሎች ከበቂ በላይ መልስ ያገኛሉ፡፡ የመለስ ራዕይ የኢህአዴግ ራዕይ የግለሰብ ወይንም የቡድን ፍላጎት ማስፈፀሚያ ሳይሆን የድፍን 80 ሚሊዮን ሕዝብ የሁልግዜም ምኞት፤ ጉጉትና ናፍቆት ራዕይም እንደሆነ ይረዱታል፡፡ ስለሆነም የመለስን ራዕይ ለማሳካት እንትጋ!!